የኢትዮጵያውያን ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ መግባባትና እርቀ ሠላም ዓለም አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ
All Ethiopian Inclusive National Consensus & Reconciliation International Co-ordinating Committee

# አስቸኳይ የእናት አገር ጥሪ

**የተጀመረውን ለውጥ ለማስቀጠል ሁሉን አቀፍ አገራዊ መግባባትና ዕርቀ ሰላም በአስቸኳይ!!**

## የካቲት 28 ቀን 2011 ዓ.ም በተደረገው ሁሉን-አቀፍ አገራዊ መግባባትና ዕርቀ-ሠላም የምክክር መድረክ ተሳታፊ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የተሰጠ የጋራ መግለጫ!!!

ከሁሉ በማስቀደም እሁድ የካቲት 30 ቀን 2011 ዓ.ም በኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራ ቁጥር 302 በደረሰው አደጋ ህይወታቸውን ላጡ ተጓዝ የ35 አገራት ዜጎች በሙሉ የተሰማንን ጥልቅ መሪር ሃዘን፣ እንዲሁም በስመ ጥሩው አየርመንገዳችን ላይ በደረሰው መጥፎ አጋጣሚ የተሰማንን ሃዘን እንገልጻለን፣ ለሟቾች ምህረትን ፣ ለሟቾች ቤተሰቦችና ወዳጆች መፅናናትን ፣ ለአየር መንገዳችን ማንሰራራትን እንመኛለን፡፡

በአገራችን የለውጥ ሂደት ከተጀመረበት አንድ ዓመት አበረታች እርምጃዎች ተወስደዋል፤ ላለፉት 26 ዓመታት በነበረው አፋኝ የጭቆና አገዛዝ ላይ በተደረገው ህዝባዊ ትግል ከኢህአዴግ ውስጥ በተወሰደው የለውጥ ኃይል እየተመራ አዎንታዊ ፖለቲካዊ እርምጃዎች ተወስደዋል፡፡ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ ጋዜጠኞችና አክቲቪስቶች ላይ ተመስርቶ የነበረው የሽብር ክስ ፍርድ ተነስቶ ከእስር መፈታት፣ በጋዜጠኞችና በፕሬስ ውጤቶች ላይ የተጣለው ስውርና ግልፅ ገደብ ተነስቶ የተሻለ የፖለቲካ ምህዳር መፈጠር፣ በአሸባሪነት የተፈረጁ፣ በትጥቅ ትግል ይታገሉና በውጪ አገር ሆነው ይንቀሳቀሱ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ አገር ቤት ገብተው እንዲንቀሳቀሱ መደረጉ፣… ወዘተ ከሕዝቡና ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ጭምር ይሁንታና ሰፊ ድጋፍ በሕዝብ ውስጥ ያጫረው ተስፋ ብዙ ከጎኑ ሥጋት እንዲከተለው እየሆነ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ህገወጥ ድርጊዎች ጅምሩ ለውጥ ነው ወይስ "ነውጥ"? የሚለው የሁሉም ወገን የፖለቲከኞችም የሕዝብም ጥያቄ እየሆነ ነው፡፡

የካቲት 28 ቀን 2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ ራስ ሆቴል በሁሉም አቀፍ ብሔራዊ መግባባትና ዕርቀ-ሠላም ሁለተኛ የምክክር መድረክ የተሳተፍን የፖለቲካ ድርጅቶች በጉባኤው ሦስት የመነሻ አጀንዳዎች አጠቃላይ ሁሉን አቀፍ ማለትም፡-

1) የህገ-መንግስት መሻሻል ጉዳይ፤
2) የለውጡ ሂደት በማን እና እንዴት ይመራ፣
3) ሁሉን-አቀፍ አገራዊ መግባባትና ዕርቅ፣

ካፀደቅን በኋላ በወቅታዊ የአገራችን አሳሳቢ ሁኔታ ኮሚቴው መግለጫ እንዲያወጣ በደረስነው ስምምነት መሰረት የሚከተሉትን የጋራ መግለጫ አውጥተናል፡፡

ይህ መግለጫም ለጉባኤው ከጸደቁ አጀንዳዎች ጋር የተገናኙ በተጨባጭ ሁኔታው በስፋትና ብዛት የሚስተዋሉትን ችግሮችና መፍትሄዎች የሚመለከት ነው፡፡

እነዚህን በሚከተሉት ጥቅል መገለጫዎችና ጭብጦች፣ ማሳየት ይቻላል፡፡

1ኛ/ በተለያዩ የአገሪቱ አካባቢዎች የተፈጠሩ ዘር ተኮር ግጭቶች ተከትሎ በጌዲኦ፣ መስቃን፣ ወላይታ፣ አማሮ፣ ቴፒ፣ ምዕራብ ኦሮሚያና ቤኒሻንጉል፣… አካባቢዎች ዜጎች በሚሊዮን ተፈናቅለው (በእነዚህ እርስ በእርስ ግጭቶች) ከ2.8 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ተፈናቅለው ለኑሮ የሰው እጅ እየጠበቁ መሆኑን ዓለም አቀፍ የነፃ ምንጭ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ለከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ተጋልጠዋ፣ ሰብዓዊ ቀውስ አስከትለዋል፡፡

2ኛ/ ህገ መንግስቱን ተከትሎ የሚነሱ የማንነት፣ የወሰንና አስተዳደር ጥያቄዎች፣ በክልል ድንበር አካባቢዎች፣ በአዲስ አበባና ኦሮሚያ ክልል፣ በደቡን ክልልና ሀዋሳ ከተማ እንዲሁም በደ/ብ/ብሕ/ብ/ክ መንግስት የዞን አስተዳደሮች የክልል ጥያቄ፣ የወልቃይት ጠገዴ፣ ራያ፣ ምዕራብ ኦሮሚያና ቤኒሻንጉል፣ሱማሌባ ኦሮሚያ፣ … አዋሳኝ አካባቢዎች፣ ለውጥረት ተዳርገዋል፡፡ የአዲስ አበባ ጉዳይ ከህገ መንግስታዊው የኦሮሚያ ልዩ ጥቅም መከበር ጥያቄ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ወደ ባለቤትነት መብት ጥያቄ ተሸጋግሯል፡፡ በደቡብ ክልል ርዕሰ ከተማ የክልሉ ገዢ ፓርቲና መንግስት መሰብሰብ ጥያቄ ውስጥ ገብቷል፡፡

3ኛ/ ህገ መንግስታዊነትና የሕግ የበላይነት መከበር አሳሳቢ ደረጃ ላይ ናቸው፡፡ ሥርዐተ-አልበኝነት ገንግኖ በአገሪቱ ህግ ምንም ህጋዊ አደረጃጀትና ዕውቅና የሌላቸው አንዳች ህጋዊ ተጠያቂነት የሚመለከታቸው የማይመስሉ ግለሰቦችና ቡድኖች በሚዲያ፣ በአክቲቪስት፣ በፖለቲካ ድርጅት ስም፣ የመከፋፈልና ጥፋት ቅስቀሳ እያደረጉ፣ አጥፊ-ፕሮፓጋንዳ እየነዙ፣ ስልፍ እያደረጉ፣ ቢሮ እየከፈቱ፣ መንግስትን ጭምር እያስፈራሩ፣… እንደፈለጉት ሲሆኑ፣ የፈለጋቸውን የነውጥ ጥሪ ሲያስተላልፉ፣ ወይም ጭፍን ድጋፍ እየሰጡ መንግስትን ሲያሳስቱ እየተመለከትን መንግስት ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድና የሕግ የበላይነት ለማስከበር ሲቸገር ወይም ሳይፈለግ እየታዘብን ነው፡፡

4ኛ/ በሰሞኑ ለገጣፎን ጨምሮ በአዲስ አበባ ዙሪያ በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች እንዲሁም በወላይታ ሶዶ ከተማ በህገወጥ ግንባር ሥም የሚደረገው የቤት ማፍረስና የዜጎች መፈናቀል፣ ይህንኑ ተከትሎ ከዜጎች ለሚነሱ ጥያቄዎች የሚሰጡ ምላሾችና በገዥው ፓርቲ የሚሰጡ ማስተባባያዎችና እርስ በእርስ የሚያጋጩ የሚመስሉ አቋሞች በእጅጉ አጠያያቂና አሳሳቢ ናቸው፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች ሲታዩ ውጤታቸው ጅምሩ የለውጥ ሂደት ላይ ባሳደረው ተስፋ ላይ ጥላ አጥልተውበት ህዝብ፣ አክቲቪስቶች፣ ባለድርሻ አካላትና ተፎካካሪ ፓርቲዎች ለለውጥ ሂደትና የለውጡ መሪዎች የሰጡትን ድጋፍ ከጥያቄ ውስጥ ከተዋል፡፡ ያልተመለሰው የትናንት ኢህአዴግ አለ/የለም የሚለው ጥያቄ ዛሬ መንግስት በተለይ የደ/ብ/ብ/ህ ክልልና የፌደራል መንግስታት አሉ/የሉም ወደሚለው አድጓል፡፡ ትናንት ስለጅምሩ ለውጥ የሚነሳው የዘላቂነትና ቀጣይነት ጥያቄ ያለነው ለውጥ ወይስ ነውጥ ጅማሮ ወደሚለው በፍጥነት ተሸጋግሯል፡፡

ከመ-እንስሶች ስላልሆንን እንደሰው በህግ መተዳደር አለብን እና የሕዝባዊ ቅቡልነቱ ጥያቄ እንዳለ ሆኖ ህገ-መንግስትና መንግስት በአለበት ሀገር የሕግ የበላይነት መጠበቅ አለበት።

ስለዚህ፡-

1ኛ/ መንግስት/ገዥው ፓርቲ በአገሪቱ የሚታየውን ግጭቶች፣ ቀውስና አለመረጋጋት መፍትሄ ለመስጠት እንደ መንግስት ከማንደርገው ጎን ለጎን በተደጋጋሚ ላቀረብነው ሁሉን-አቀፍ አገራዊ መግባባትና ዕርቀ-ሠላም ሁሉን አቀፍ ጉባኤ ጥሪ አስቸኳይ ምላሽ በመስጠጥ ዘላቂ መፍትሄ እንድንፈልግ እንዲደረግ፣

2ኛ/ በህገመንግስቱ ላይ የሚነሱት ጥያቄዎች እስከሚመረመሩና እስከሚስተካከሉ ድረስ የሕግ የበላይነት ተከብሮ ከህግ አግባብ ውጪ ዜጎች በህገወጥ ግንባታ ስም ማፈናቀልና ከህግ ውጪ የሚደረጉ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች በአስቸኳይ እንዲገቱ፣

3ኛ/ የተጀመረው የለውጥ ሂደት እንዳይደናቀፍና እንዳይቀለበስ፣ ሲያልፍም ወደ ነውጥ እንዳይለወጥ ሁሉም ባለድርሻ አካላት እንዲረባረቡ እንዲጠበቁ

4ኛ/ መላው የአገሪቱ ህዝብ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ተቋማት፣ ህዝባዊና የሙያ አደረጃጀቶች፣ የኃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሎዎች፣ የባህል መሪዎች፣ አክቲቪስቶችና ልሂቃን፣… ከሁሉም በላይና በፊት የሠላምና የአገሬ ጉዳይ ያገባኛል በሚል የኃላፊነት ስሜት፣ ዴሞክራሲያውም፣ መብቱም ዕድገትና ልማቱ በሠላምና አገር ስትኖር ስለሆነ ለወቅቱ የአገራችን አሳሳቢ ሁኔታ በረጅም ዘመን የተዘራውን የዘርና መከፋፈል አረም ነቅለን ከልዩነታችን በእጅጉ በሚልቁት አንድ በሚያደርጉን አገራዊ ጉዳዮቻችን መግባባት ፈጥረን ዕርቅ አውርደን፣ በጋራ በምንቀምበት አጀንዳ በንቃት በመሳተፍ የመፍትሄው አካል እንዲሆኑ፣

5ኛ/ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ አገርና ህዝብ ከየትኛውም የፖለቲካ ድርጅትና ካለው መንግስት በላይ በመሆኑ፣ ጥቅማቸውን የሚያስከብሩትና የሚከበረው አገር ሰላም ስትሆን፣ ህዝቡ በተረጋጋ ሁኔታ ሲኖርና ሲያመርት፣ ጤናማ ማህበረ-ኢኮኖሚና ፖለቲካ ከባቢ ሲፈጠር ስለሆነ አስላለፋቸውን ከሕዝብ ጎን እንዲያደርጉና በመንግስት/ገዥው ፓርቲ ላይ በሚመለከታቸው ልክ አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዲያሳርፍ ጥሪያችንን እናቀርባለን። ለተግባራዊነታቸውም በህብረት እንታገላለን።

«የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት፣ አንድነትና ክብር በልጆቿ መስዋዕትነት ይጸናል!!!»

«አንዲት ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!»

ፈጣሪ አገራችንንና ህዝባችንን ይባርክ

መጋቢት 06 ቀን 2011 ዓ.ም፣አዲስ አበባ

## የምክክር መድረኩ ተሳታፊዎችና መግለጫው እንዲወጣ የተስማሙ የፖለቲካ ድርጅቶች፤

1. አዲስ ትውልድ ፓርቲ (አትፓ)
2. ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ (ቅንጅት)
3. ኦሮሞ ነፃነት ብሔራዊ ፓርቲ (ኦነብፓ)፤
4. የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት ኮንግረስ ፤
5. የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)፤
6. የኢትዮጵያዊያን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ)፤
7. አንድ አገር ፤አንድ ህዝብ ኢትዮጵያችን ህዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን)፤
8. የኢትዮጵያ ዲሞክራቲክ ኀብረት (ኢዲኀ)፤
9. የወላይታ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ወህዴግ)፤
10. የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ (ኢዲአን)፤
11. የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግሬስ (ኦብኮ)፤
12. የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ (ኢራፓ)፤
13. የአፋር ህዝብ ፍትህ ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (አህፍዴፓ)፤
14. መላው ኢትዮጵያ ብሄራዊ ንቅናቄ (መኢብን)፤
15. መላው ዐማራ ህዝብ ድርጅት (መዐህድ)፤
16. የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት ፓርቲ (ኢብአፓ)፤
17. ምክክር ለአንድነት ዲሞክራሲ ፓርቲ (ምክክር)፤
18. የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር (አርበኞች)፤
19. ደንጣ ዱባሞ ክችንችላ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ደዱክህዲድ)፤
20. ነጻነት ለአንድነት ድርጅት፤
21. አማራ ህልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (አህኢአድ)፤
22. የዶንጋ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፤
23. ቱሣ የኢትዮጵያ ትንሳኤ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ቱሣ)፤
24. የትግሬ ወርጂ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት፤
25. የኦሮሞ አንድነት ነጻነት ግንባር (ኦአነግ)፤
26. የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)፤

27. ሸንጎ፣

28. የኦሞ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ኅብረት (ኦህዲኅ)፣

29. የመላው ኢትዮጵያዊያን ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (መኢዴፓ)፣

30. የኦሮሞ ነጻነት ንቅናቄ (ኦነን)፣

31. የአፋር ህዝብ ነጻነት ፓርቲ (አህነፓ)፣

32. ገዳ-ሥርዓት አራማጅ ፓርቲ (ገዳ)፣

33. ነጻነት ለአንድነት ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ/፤

34. ጋሻ የአማራ መድንን ቅናቄ፤

35. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሽግግር ምክር ቤት (ሽግግር)፣

36. የከንባታ ህዝብ ኮንግረስ (ከህኮ)፣

37. የሥልጤ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ስህዴፓ)፣

38. የጌዴኦ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ጌህዴድ)፣

39. ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ሉዓላዊነት (ዓረና)፣

40. የኢትዮጵያዊውያን ሀገር አቀፍ ንቅናቄ (ኢሀን)፣

41. የቤንሻንጉል ሕዝብ ነፃነት ንቅናቄ ለሠላምና ዴሞክራሲ፣

42. ሲዳማ ሀዲቾ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፣

43. የአገው ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አገዴፓ)፣

44. የሲዳማ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ፣

45. የኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣

የኢትዮጵያውያን ሁሉን አቀፍ ብሔራዊ እርቀ ሠላም ዓለም አቀፍ አስተባባሪ ኮሚቴ
All Ethiopian Inclusive national consensus & reconciliation international co-ordinating committee
የአገር ቤት ኮሚቴ አዲስ አበባ
Homeland Committee Addis Ababa